የመከላከያ ሰራዊት አባሎች በወያኔ ሹማምንት ላይ ተቃውሞ አሰሙ፤

መለስ ዜናዊ ለጄኔራሎቹ የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ መስጠቱ ፤

የፌዴራል ፖሊስ ከፍተኛ ባለስልጣናት በምስጢር ናዝሬት ላይ ለሁለት ቀን ዝግ ስብሰባ ማድረጋቸው፤

በእውቁና እንቁው አርቲስት ጥላሁን ገሠሠ ስርዓተ ቀብር እለት በርካታ ሰዎች ላይ ድብደባ ተፈፀመ፤

ብዙዎች ታፍሰው ወዳልታወቀ ስፍራ ተወሰዱ፤

የሙስሊም እምነት ተከታይ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች በፌዴራል ፖሊስ ድብደባ ተፈፀመባቸው- ብዙዎቹ ሆስፒታል ገቡ፤

የሱዳኑ ፕሬዝዳንት አልበሽር ከወያኔ ጋር ምስጢራዊ ስምምነት መፈረሙ ታወቀ፤

EthioLion.Com

የመከላከያ ሰራዊት አባሎች አመፅ መጀመራቸውን ከተለያዩ ግንባሮች የደረሳቸውን ጥቆማ ዋቢ በማድረግ የመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች አጋለጡ፡፡በተለያዩ የሀገሪቱ ግንባሮች ሰፍረው ያሉት የጦሩ አባሎች በሚፈፀምባቸው አድልኦና በደል የተነሳ ተደጋጋሚ ጊዜ እንዲሻሻል አቤቱታና ጥሪ ቢያቀርቡም ሰሚ ካለማግኘታቸውም በላይ በቅርቡ ደግሞ ከአስር ዓመት በላይ ያገለገሉ አባሎችን ከስራ በመቀነሳቸው የጦሩ አባሎች በአለቆቻቸው ላይ አመፅ ማንሳታቸው ታወቀ፡፡

በጦሩ መሀከል ችግር ሊፈጥሩ ይችላሉ የተባሉትን ከየጦሩ ክፍል ለቅመው ለእስር ከዳረጉ በሁዋላ ባለፈው ሳምንት ውስጥ በሺህዎች የሚቆጠሩትን ከምስራቅ ግንባር በማባረራቸው የተናደዱት በስራ ላይ ያሉት የጦሩ አባሎች በቅርብ አለቆቻቸው ላይ ከማመፃቸውም በተጨማሪ  የእዙ አዛዥ መጥቶ እንዲያነጋግረን እንፈልጋለን በማለት ማመፃቸውን የመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች አጋልጠዋል፡፡

በምስራቅ እዝ ስር ያለው ጦር ብዙ ዓመታት በበረሀ ሲንከራተት የኖረ ሲሆን በተለያዩ ጊዜያት በሰራዊቱ ላይ የሚፈፀመው አድልኦና ግዴለሽ አሰራር እንዲቀረፍ ቢገልጹም ሊሻሻል ካለመቻሉም በላይ ይህ ጥያቄ በጦሩ መሀከል እንዲሰርፅ ያደረጉ ናቸው የተባሉ በሺህዎች የሚቆጠሩ አባሎች የአገልግሎት 9 ሺህ ብር እየተሰጣቸው ከስራ እንዲሰናበቱ በመደረጋቸው የተበሳጩት በስራ ላይ ያሉት የጦሩ አባሎች በየሰፈሩበት ካምፕ ውስጥ ተኩስ በመክፈት የቅርብ አለቆቻቸውን ከማስፈራራታቸውም በተጨማሪ የእዙ አዛዥ መጥቶ እንዲያነጋግራቸው አስቸኩዋይ ጥሪ ማቅረባቸው ታውቆዋል፡፡

የጦሩ አባሎች ባቀረቡት ጥሪ መሰረት የምስራቅ እዝ ዋና አዛዥ ሜ/ጄ/ል ገብረእግዚአብሔር መብርሀቱ በአካል ተገኝቶ ያነጋገራቸው ቢሆንም ከዚህ ቀደምም ጥያቄ ሲያቀርቡ የሚሰጣቸውን የመሸንገያ መልስ በመስጠቱ የተናደዱት ወታደሮች ስብሰባውን  ትተው  በመሄዳቸው የተደናገጠው ይኸው ጄኔራል መኮንን የጦሩ አባሎችን ሲማፀን እንደነበረ ምንጮቹ አስረድተዋል፡፡

ከ10 ዓመት በላይ በረሀ ለበረሀ፤ ቆንጥር ለቆንጥር ቀን በሀሩር ለሊት በውርጭ እየተጠበስን ዳር ድንበር ባስከበርን በእኛ ላይ እየተሰራ ያለው አድልኦ የሚያሳዝን ነው ያሉት የጦሩ አባሎች በተለይ ለሰላም ማስከበር ምርጫ ሲደረግ የዘር ሀረግ መሰረት አድርጋችሁ መሆኑን ያወቅነው ዛሬ ባይሆንም ስር እየሰደደ በመምጣቱ ለዚህ ድርጊት የምትሰጡት ምላሽ ምንድነው? በቅርቡስ ከስራቸው ላይ የተሰናበቱት የጦሩ አባሎች ያጠፉት ጥፋት ምንድነው? የሚሉና ሌሎችም በርካታ ጥያቄዎች አቅርበው ያነጋገሩት ሲሆን ሜ/ጄ/ል ገ/እግዚአብሄር የተባለው የወያኔ የጦር መኮንን ምላሽ  ለመስጠት ተቸግሮ እንደበቱ በድንጋጤ ተወለካክፎ መናገር ተስኖት ከቆየ በሁዋላ ይህንን ጉዳይ

EthioLion.com

ከበላይ አለቆች ጋር መክሬ መልስ እሰጥበታለሁ ሲል እየተማፀነ እንደነበር ምንጮቹ አጋልጠዋል፡፡

በጄኔራሉ ምላሽ ያልተደሰቱት ወታደሮች ከእንግዲህ እኛ ወታደሮች አይደለንም እያሉ ጥይት ወደ ሰማይ እየተኮሱ ከስብሰባው ቦታ ጥለው ሲወጡ ይኸው የእዙ አዛዥ ጄኔራል እስከ ዛሬ ድረስ ጨርቅ ሲል ሲያንቆዋሽሽ እንዳልነበረ የኢትዮጵያን ባንዲራ ይዞ እያነባና በጉልበቱ ተንበርክኮ በኢትዮጵያ አምላክ እያለ ሲለምናቸው እና ሲማፀናቸው እንደነበረና ጦሩም ከቁጣው በረድ ለማለት እንደቻለ ምንጮቹ አጋልጠዋል፡፡

በምስራቅ እዝ የተጀመረው የሰራዊቱ አመፅ ሽሬ ሰፍሮ ወደሚገኘው ማዕከላዊ እዝ ተሸጋግሮ ተመሳሳይ ችግር የተፈጠረ ሲሆን እዚያም የጦሩ አባላት ላቀረቡት ጥያቄ የእዙ ምክትል አዛዥ ብርጋዴየር ጄኔራል ማእረግ ያለው መኮንን ምላሽ ለመስጠት ቢሞክርም አጥጋቢ መልስ ካለመስጠቱም በላይ በተሰጣቸው መልስ ያልተደሰቱ በመሆኑ ዋና አዛዡ እንዲቀርብ በድጋሚ ጥያቄ በማቅረባቸው ለእረፍት ከሄደበት ባስቸኳዋይ ተጠርቶ እንዳነጋገራቸው ከምንጮቹ ገለጻ ለመረዳት ተችሎዋል፡፡

ለእረፍት ከስራ ውጭ ሆኖ የነበረው የማዕከላዊ እዝ አዛዥ ሌ/ጄ/ል አበባው ታደሰ ካለበት ተፈልጎ እንዲመጣ ከመደረጉም በላይ ጦሩ ላነሳው ጥያቄ መሸንገያ ምላሽ በመስጠት ለጊዜው ችግሩ ሊፈታ የቻለ ቢሆንም የጦሩ ልብ ከዕለት ወደ ዕለት እየሸፈተ በመሆኑ ሌላ አዲስ ስልት ለማዘጋጀት እቅድ ወጥቶ ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑንም ምንጮቹ አብራርተዋል፡፡

በምስራቅ እዝ እና በማዕከላዊ እዝ ውስጥ የተከሰተው የሰራዊቱ አመጽ ወደ ሌሎች የጦር ክፍሎች እንዳይዛማት እና ወደ ሌላ አቅጣጫ እንዳቀየር በሚል ስጋት የወታደራዊ ልብሶችን እና ጫማዎችን ያደሉዋቸው ከመሆኑም በላይ በያቅራቢያቸው በሚገኙ ከተሞች ለሁለት ለሁለት ቀናት እረፍት አድርገው እንዲመጡ በየክፍሉ እንደተፈቀደላቸው ተገልፆዋል፡፡

በአሁኑ ሰዓት ጦሩ ከነ ሙሉ ትጥቅ ያለ በመሆኑ እና አመጹን ከገፋበት ከፍተኛ ችግር ሊፈጠር እንደሚችል ስጋት የገባቸው የወያኔ ጄኔራሎች በዘዴ ትጥቅ ማስፈታት አማራጭ መሆኑን ቢያምኑም ሰራዊቱ ደግሞ ትጥቁን ለመፍታት ፍቃደኛ ባለመሆኑ ፍርሀት እና ስጋት ውስጥ መግባታቸውንም ምንጮቹ አጋልጠዋል፡፡

በእንዲህ ያለ ውጥረት ውስጥ ያሉት እነ ጄኔራል ሳሞራ የኑስ በየአቅጣጫው ችግሩን ለመፍታት ባቃታቸው ወቅት የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ በበኩሉ እቢሮው ድረስ አስጠርቶዋቸው « በእናንተ እንዝህላልነት ያበላሻችሁትን ስራ እና ሊፈጠር የሚችለውን አደጋ ሳታስተውሉ እየተዝረከረካችሁ ለዚህ ያበቃችሁት እናንተ ስለሆናችሁ በእስቸኳዋይ አስተካክላችሁ ሪፖርት እንድታደርጉ »በማለት የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ መስጠቱንም ምንጮቹ አጋልጠዋል፡፡

EthioLion.Com

በዚህም የተደናገጡት ጄኔራል ተብዬ የመሀይም ጥርቅሞች በ1990ዎቹ መጀመሪያ ላይ እንደተደረገው «ተሀድሶ» በሚል የጦሩን አባላት በየቦታው እየከፋፈሉ ግምገማ ማድረግ እና የፖለቲካ ትምህርት መስጠት እና አንገት ማስደፋት ዋና አዋጭ መፍትሄ ነው ብለው ስላመኑበት ግምገማውን የሚመሩትን እና ለስርዓቱ ቅርበት አላቸው የተባሉት ከየጦር ክፍሎች ውስጥ እየመለመሉ አምጥተው ስልጠና ለመስጠት እንቅስቃሴ መጀመሩ ታውቆዋል::

የጦሩን አባላት ከዚህ ቀደም እንደታየው ሁሉ ግምገማ በሚል የተነሱትን ጥያቄዎች ማፈን እና በጦሩ የተጀመረው አመጽ አከርካሪውን ለመምታት እንዲያመቻቸው ቅድሚያ ለአንድ ሳምንት በአዲስ አበባ ውስጥ ኮርስ ለሚሰጣቸው ገምጋሚዎች ኮርስ መስጠት እና ፖለቲካ ማጥመቅ ግድ ስለሚል ከሚያዚያ 16 ቀን 2001 ዓ. ም. ጀምሮ ስልጠና መግባታቸው ታውቆዋል::

ሠራዊቱን በመቶ፤በጉዋድ፤በሻምበል፤ በሻለቃ ደረጃ ከፋፍለው እና ነጣጥለው በግምገማ ሰበብ ለመምታት የተጀመረው ስልት ተግባራዊ መሆን የሚጀመረው ከዚህ ወር ማብቂያ ጀምሮ ሲሆን በተጉዋዳኝ ሌሎች የሰራዊቱን እንቅስቃሴ የሚገድቡና አንገቱን የሚያስደፉ ስልቶችን ለመጠቀም ውስጥ ውስጡን ዘመቻ መጀመራቸውም የመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች ገልፀዋል::

በዚህና በመሳሰሉት ጉዳዮች ላይ የተወጠሩት የወያኔ ጄኔራሎች ለአራት ቀናት በምስጢር በመኮንኖች ስብሰባ አዳራሽ ውስጥ ሲነታረኩ መሰንበታቸውም የታወቀ ሲሆን ስብሰባው በጄ/ል ሳሞራ የኑስ የሚመራ መሆኑም ከምንጮቹ ጥቆማ ለማወቅ ተችሎዋል::

ዝግና ምስጢራዊ ስብሰባው ላይ የተገኙት የጦር ጄኔራሎች ተመርጠው ሲሆን እነሱም ጄኔራል ሳሞራ የኑስ የጦር ኃይሎች ኢታማዦር ሹም፤ሌ/ጄ/ል ታደሰ ወረደ በአሁን ሰዓት በመከላከያ ከሳሞራ ቀጥሎ የተቀመጠ በመሆኑ፤ሌ/ጄ/ል ሳዓረ መኮንን የሰሜን እዝ ዋና አዛዥ በመሆኑ፤ሌ/ጄ/ል አበባው ታደሰ የምዕከላዊ እዝ ዋና አዛዥ በመሆኑ፤ሜ/ጄ/ል ስዩም ሀጎስ የምዕራብ እዝ ዋና አዛዥ በመሆኑ፤ሜ/ጄ/ል ገብረ እግዚህአብሄር መብርሀቱ የምስራቅ እዝ አዛዥ እና ዋና የጦሩ ሰለባ ሊሆን የነበረ በመሆኑ፤ሜ/ጄ/ል ገዛኢ አበራ የመከላከያ የሎጀስቲክ መምሪያ ኃላፊ በመሆኑ፤ሜ/ጄ/ል ሞላ ኃይለማሪያም የአየር ኃይል ጥብቅ አዛዥ በመሆኑ ምስጢራዊ ስብሰባው ላይ ተገኝተዋል::

ችግሩን ቀርፋችሁ በአስቸኩዋይ ሪፖርት አድርጉልኝ ብሎ መለስ ዜናዊ የሰጠውን ትዕዛዝ ተፈፃሚ ለማድረግ ከላይ እታች እየባዘኑ ከመሆኑም በተጨማሪ በዝግ ስብሰባ ብቻቸውን ሲነታረኩ እንደሰነበቱም የውስጥ አዋቂ ምንጮቹ አስረድተዋል::

EthioLion.com

በዚሁ ዝግ ስብሰባ ላይ አንዱ የተነሳው በቅርቡ ጦሩን ሲያነሳሱ ነበር ተብሎ ከየክፍላቸው ታፍሰው ለእስር የተዳረጉት መኮንኖች ዙሪያ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት በተለያዩ እስር ቤት ውስጥ ታጉረው የሚገኙ ቢሆንም አሁን የተነሳውን የጦሩን አመፅ ለማብረድ እንዲያመች እና ተስፋ ለማስቆረጥ የታሰሩት ላይ የመከላከያ የጦር ፍርድ ቤት አስፈላጊውን ቅጣት እንዲወስን ሁሉም በአንድ ድምጽ መወሰናቸው እና መስማማታቸው ታውቆዋል::

የአፍሪካ ህዝብ ኩራት እና መለያ የሆነውን የኢትዮጵያ ባንዲራ እስከ ዛሬ ድረስ ጨርቅ ነው እያሉ  ሲያጣጥሉት እንዳልነበረ ዛሬ ጦሩ በሚደርስበት በደልና ግፍ ተማርሮ እርምጃ ለመውሰድ በተነሳሳበት ወቅት ባንዲራ እያነጠፉ ልመና ማቅረባቸው እጅግ አስገራሚና አታላዮች መሆናቸውን በጉልህ ያጋለጠ መሆኑም ታውቆዋል::

በተያያዘ ዜና በመከላከያ ሰራዊት ውስጥ የተጀመረው የመብት ጥያቄ እና በአለቆቻቸው ላይ ያነሱት አመጽ ወደ ፌዴራል ፖሊስ አባሎች ውስጥ ይዛመታል ተብሎ ስጋት በማሳደሩ የተነሳ አስቸኩዋይ መፍትሄ ለማዘጋጀት በሚል የፌዴራል ፖሊስ ከፍተኛ ባለስልጣናት በምስጢር ስብሰባ ላይ መሰንበታቸው ታወቀ::

ከሚያዚያ 13 ቀን እስከ ሚያዚያ 15 ቀን 2001 ዓ.ም. ድረስ ለሶስት ቀናት በናዝሬት ከተማ በድብቅ የፌዴራል ፖሊስ ከፍተኛ ባለስልጣናት በስውር እና በምስጢር ስብሰባ ሲያደርጉ የሰነበቱ ሲሆን በመከላከያ እየተስተዋለ ያለው አስቸጋሪ ሁኔታ ወደ ፌዴራል ፖሊስ ውስጥ እንዳይዛመት እና እንዳይዘልቅ ለማድረግ አስቀድሞ ለመከላከል የተዘጋጀ መሆኑን የውስጥ አዋቂ ምንጮቹ ገለፃ አስረድቶዋል::

በተለይም በሰራዊቱ ውስጥ የተነሳው አመጽን ተከትሎ በፌዴራል ፖሊስ አባሎች ዘንድም አለቆቻቸውን መግደል መጀመራቸው ሌላው የተቃውሞ መግለጫ በመሆኑ  ባጭሩ ለመቅጨት እና ፖሊስ አድርግ የሚባለውን ብቻ እንዲያደርግና እንደጋሪ ፈረስ እንዳሻቸው ለማድረግ በሚቻልበት  ሁኔታ ለማስተካከል እንደሆነም የምንጮቹ ገለፃ አስረድተቶዋል::

በአሁኑ ሰዓት የፌዴራል ፖሊስ ከ60 ሺህ በላይ በሀገሪቱ የተለያዩ ክልሎች ውስጥ ሰፍሮ እንደሚገኝም ምንጮቹ ጠቁመዋል::

የእውቁ አርቲስት ጥላሁን ገሠሠ ስርዓተ ቀብር በሚፈፀምበት  እለት በርካታ ሰዎች በፌዴራል ፖሊሶች ድብደባ እንደተፈፀመባቸው ታወቀ::  ሐሙስ ሚያዚያ 16 ቀን 2001 ዓ. ም. የእውቁ ድምጻዊ አርቲስት ዶክተር ጥላሁን ገሠሠ  ቀብር በቅድስት ስላሴ ቤተክርስቲያን ወዳጅ ዘመድ፤ ሀገር ወዳድ ዜጎች በተገኙበት ለመፈፀም በተቃረበበት ወቅት መስቀል አደባባይ ላይ ለቀብር የተሰበሰበውን ህዝብ ሆን ብለው ነገር ፈልገው የፌዴራል ፖሊሶች ድብደባ የፈጸሙባቸው ከመሆኑም በተጨማሪ ብዙዎቹን

EthioLion.Com

ሲቪል የለበሱ የክትትል ሰራተኞች እና ደህንነቶች እያፈኑ ወዳልታወቀ ስፍራ መውሰዳቸው ታውቆዋል::

የቀብሩ ስነስርዓት በአግባቡ አለምን ጉድ ባሰኘ መልኩ ለመፈፀም በተዘጋጀበት ወቅት ለመበጥበጥ እና ሰይጣናዊ አላማቸውን ለማሳካት የሚሩዋሩዋጡት የፌዴራል ፖሊስ ኃይሎች ገና አስከሬኑ ከመስቀል አደበባባይ ሳይነሳ «ጥላሁን ተለየን» የሚል ዜማ ህዝቡ በመቀባበል ላይ እንዳለ ሆን ብለው ለምን ትጮሀላችሁ እያሉ ከየመሀሉ እየመረጡ ድብደባ የጀመሩ ከመሆኑም በተጨማሪ አንዳንዶቹን እያፈኑ ወደ ያልታወቀ ስፍራ ይዘዋቸው መሰወራቸውን ለማየት ተችሎዋል::

በጥላሁን ሞት ልቡ በሀዘን የተቆራመደውን ህዝብ ሆን ብለው የነገር መርዝ እየረጩ እንዲነሳሳ እና እንዲበጠበጥ ለማድረግ ቢሞክሩም ህዝቡ አለምን ባስደነቀ ሁኔታ ስርዓተ ቀብሩ እንዲካሄድ በማሰቡ አይቶ እንዳላየ ሰምቶ እንዳልሰማ በመሆን በትእግስት ለማሳለፍ ሙከራ ቢያደርግም ከአቅሙ በላይ በመሆኑ ከፌዴራል ፖሊስ ጋር ግጭት ሊፈጠር እንደቻለም ታውቆዋል::

ከ1997 ዓ. ም ወዲህ ለመጀመሪያ ጊዜ በመቶ ሺህዎች በአደባባይ ወጥቶ የታየበት ወቅት በመሆኑ የተደናገጡት የወያኔ ፌዴራል ፖሊሶች ባለባቸው ውስጣዊ ስጋት የተነሳ ህዝቡን ከማስፈራራታቸውም በተጨማሪ በነገር እየተነኮሱ እና ሁከት እንዲነሳ ለማድረግ ቢጥሩም በህዝቡ አርቆ አስተዋይነት በአጭሩ ሊከሽፍ የቻለ ቢሆንም በብዙ ሰዎች ላይ ከፍተኛ ድብደባ መፈጸሙ ግን ታውቆዋል::

ገና አስከሬኑ ሳይነሳ በመስቀል አደባባይ እንዳለ «ተዲ ይፈታ! አደራ ተረካቢው ቲዲ ነው!» የሚሉና ሌሎችም መፈክሮች በህዝቡ በተለይ በወጣቱ መነገር ሲጀመር ያቃጠላቸው እና ያንገበገባቸው የፌዴራል ፖሊሶች እና ደህንነቶች ጭፍን በሆነ መልኩ ድብደባ መፈጸማቸው ሲታወቅ አንዳንድ ከውጭ ሀገር የመጡ ሰዎች ድርጊቱን በስውር ካሜራ መቅረጻቸውም ታይቶዋል::

አስከሬኑ ከመስቀል አደባባይ ተነስቶ ወደ አራት ኪሎ በመጉዋዝ ላይ እንዳለ በህዝቡ ብዛት የተደናገጡት የወያኔ የፌዴራል ፖሊሶች የታችኛውን ቤተ መንግስት ዙሪያውን በተጠናከረ ጥበቃ የተቆጣጠሩት ቢሆንም ባደረባቸው ስጋት ምክንያት በስተግራ በኩል ማለፍ ክልክል ነው በማለት የከለከሉ ቢሆንም ህዝቡ በአንድ አቅጣጫ ብቻ መጉዋዝ ስለማይችል የፌዴራል ፖሊስን ትዕዛዝ ጥሰው በመሄዳቸው ግጭት ተፈጥሮ በርካታ ወጣቶች የተጎዱ ሲሆን ቀላል የማይባሉ ፖሊሶችም መጎዳታቸው ታውቆዋል::

ወያኔ ከጊዜ ወደ ጊዜ ህዝብን እየፈራ ባለበት በዚህ ወቅት በመቶ ሺህዎች የሚቆጠረውን ሀዘንተኛ በአግባቡ የእውቁን አርቲስት ጥላሁን ገሠሠ ስርዓተ ቀብር

EthioLion.Com

እንዳይፈፀም ብዙ መሰናክሎችን በተለያዩ ቦታዎች በመፍጠር ግጭቱ የተፈጠረ ቢሆንም በህዝቡ ታጋሽነት የተፈራውን ያህል ጉዳት አለመድረሱም ታውቆዋል::

በአራት ኪሎ ቅድስት ስላሴ ቤተክርስቲያን ግቢ ውስጥም ህዝቡ በተለይ ወጣቱ ለጥላሁን የስንብት ለቅሶ በሚያደርግበት ወቅት እግረ መንገዳቸውን «ቲዲ ይፈታ » እያሉ ጩኸት በማሰማታቸው የፌዴራል ፖሊሶችና ደህንነቶች ድብደባ ከመፈጸማቸውም በላይ እያፈሱ መውሰዳቸውም ታይቶዋል::

የእውቁ አርቲስት ጥላሁን ገሠሠ ቀብር ስርዓት በሀገራችን ብቻ ሳይሆን በዓለም ላይ እስከ ዛሬ ባልታየ ሁኔታ እጅግ በደመቀና ቁጥሩ በመቶ ሺህዎች ህዝብ በተገኘበት የተፈፀመ ሲሆን የወያኔ ካድሬዎች ሲሞቱ ለመገነዝ እና ለመቅበር ሲሮጡ የሚገኙት የመለስ ዜናዊ ነፍስ አባት እሳቸውም እንደልጃቸው በፍርሀት በቀብሩ ላይ ሳይገኙ መቅረታቸው ታረጋግጦዋል::

ብርቅዬው ፤ አንጋፋውና እውቁ ድምፃዊ ጥላሁን ገሠሠ በ1933ዓ. ም. በአዲስ አበባ ተወልዶ በ68 ዓመቱ እዚሁ አዲስ አበባ የሞተ ሲሆን የ12 ልጆች አባት እንደሆነም ከህይወት ታሪኩ ለመረዳት ተችሎዋል::

በተመሳሳይ ዜና የእስልምና ተከታይ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ላይ የፌዴራል ፖሊስ ከፍተኛ ድብደባ መፈጸሙ ታወቀ::አርብ እለት ሚያዚያ 17 ቀን ከቀኑ 7 ሰዓት ሲሆን መፈክሮችን አንግበው መነሻቸውን ትልቁ አንዋር መስጊድ አድርገው ወደ አራት ኪሎ በመጉዋዝ ላይ እያሉ ራስ መኮንን ድልድይ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ሲደርሱ የፌዴራል ፖሊሶች ዙሪያቸውን ከብበው በፖሊስ ዱላ ከፍተኛ ድብደባ የፈፀሙባቸው መሆኑ ታውቆዋል::

በቅርቡ የወያኔ የትምህርት ሚኒስቴር በእስልምና እና በክርስትና እምነት ተከታይ ተማሪዎች ላይ ያወጣውን መመሪያ በመቃወም የእስልምና እምነት ተከታይ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ ከአንዋር መስጊድ ተነስተው ወደ አራት ኪሎ ፓርላማ እና ትምህርት ሚኒስቴር አቤቱታቸውን ለማቅረብ ቢሞክሩም ራስ መኮንን ድልድይ ጋ ሲደርሱ ድንገት በፌዴራል ፖለሶች ተከብበው እጅግ ዘግናኝ በሆነ መልኩ ሴት ልጅ በማትመታበት ቦታ ሁሉ ሳይቀር ከፍተኛ ድብደባ የተደረገባቸው ከመሆኑም በላይ እዚያው አቅራቢያ በሚገኘው ጅንአድ ግቢ ውስጥ አስገብተው እንደዘገባቸው ለማየት ተችሎዋል::

ያደረጉትን ጫማ ሁሉ እንዲያወልቁ ተደርጎ አራት ኪሎ ዶርዜ ሀይሎ ተብሎ በሚጠራው አጠገብ በሚገኘው ጅንአድ ግቢ አስገብተው ድብደባ የፈፀሙባቸው ከመሆኑም በተጨማሪ «ከእንግዲህ በሁዋላ በየትኛውም ሰላማዊ ሰልፍ ላይ ብገኝ አስፈላጊው ቅጣት ይፈፀምብኝ »የሚል የተዘጋጀ ፎርም ላይ በግዳጅ እንዲፈርሙ ተደርጎ ከቀኑ ሰባት ሰዓት ተኩል የታሰሩ ከምሽቱ አንድ ሰዓት ላይ የተፈቱ ሲሆን

EthioLion.Com

ሰላማዊ ሰልፉን ያስተባበሩ ናቸው የተባሉ አምስት ተማሪዎች ግን ተመርጠው መታሰራቸው ታውቆዋል::

የእስልምና ተከታይ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች የትምህርት ሚኒስቲር ያወጣውን ህግ በመቃወም ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግና አቤቱታ ለማሰማት ቢሞክሩም ያልተሳካላቸው ከመሆኑም ሌላ ህገ ወጥ በሆነ መልኩ ምላሽ የተሰጣቸው በመሆኑ ህዝቡን እንዳሳዘነ ለመረዳት ተችሎዋል::

በወቅቱ በድብደባ እራሳቸውን የሳቱ እና ተደጋግሞ ማህፀናቸው በዱላ ብዛት የተጎዱ ተማሪዎች ወደ የካቲት 12 ሆስፒታል ተወስደው እንዲተኙ የተደረገ ሲሆን ይህ ዘገባ እስከተጠናቀረበት ቅዳሜ እለት ድረስ ከሆስፒታሉ እንዳልወጡ ለማወቅ ተችሎዋል::

የሱዳኑ ፕሬዝዳንት ዑመር አልበሽር አለም አቀፉ ፍርድ ቤት የእስር ማዘዣ ካወጣበት በሁዋላ ለጉብኝት በሚል ለሁለት ቀናት ቆይታ ለማድረግ አዲስ አበባ እና መቀሌ ደርሶ መመለሱ ታወቀ::

አልበሽር ወደ ሀገር ውስጥ ገብቶ ከወያኔ ጋር ገደብ የለሽ ሁሉ አቀፍ ስምምነት የተፈራረመ ሲሆን በተለይ ከኢትዮጵያ ከፍተኛ ሜጋዋት የኤሌክትሪክ ኃይል የሚወስድ ሲሆን ወያኔም በበኩሉ ነዳጅ ከሱዳን እየጫነ በማስገባት ላይ ቢሆንም ከዚህ የበለጠ የኤሌክትሪክ ኃይል ለመውሰድ የሚያስችል ስምምነት ማድረጋቸው ታውቆዋል::

አልበሽር ሁሉ አቀፍ ስምምነት ከማድረጉም በተጨማሪ በምስጢር ወደ ትግራይ አምርቶ የሰማዕታት ሀውልትን የጎበኘ ከመሆኑም በተጨማሪ ከትግራይ ክልል ጋር በተናጠል ምስጢራዊ ስምምነት አድርጎዋል::

አልበሽር በምስጢር ከተስማማባቸው አንደኛው ጉዳይ በኢትዮጵያ ህዝብ ሀብት እየተሰራ ባለው የተከዜ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ላይ ሲሆን ይህ የተከዜ ግድብ ስራው ተጠናቅቆዋል እየተባለ በወያኔ ቢለፈፍም ስራው ከማቆሙም በላይ ወደፊትም የተከዜ ጉዳይ ገና ስራ ላይ ሊውል እንደማይችል ባለሙያዎች እየገለፁ ባለበት ወቅት ከሱዳን ጋር በምስጢር ስምምነት ከትግራይ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ጋር መስማማታቸው እጅግ አስገራሚ ነው ተብሎዋል::

የአልበሽር የእስር ማዘዣ መውጣትን ተከትሎ የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ በዘር ፍጅት የአለም አቀፉ ጀኖሳይድ ዎች እንዲከሰስ አቤቱታ ካቀረበበት ወዲህና እንግሊዝ ሀገር ሄዶ በውርደት ከተመለሰ በሁዋላ ሰሞኑን በሀገር ውስጥ አንዳንድ እርምጃዎች መውሰድ መጀመሩ እየታየ ነው::

በተለይ በመከላከያ መዋቅር ላይ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ሲሆን አዲስ ወታደሮችን እያስመረቀ ሌሎች ነባሮችን ደግሞ ከስራ እያሰናበተ ከሚያደርጋቸው

EthioLion.Com

እንቅስቃሴዎች አንዱ ሲሆን ሌላው ነባር ፖለቲካ ካድሬዎቹን እያገለለ አዳዲስ ካድሬዎቹን ደግሞ እያሰባሰበ መሆኑም ታውቆዋል፡፡

ከሁለቱ ቡድኖች ስምምነት ዋነኛው የመከላከያ ሲሆን በዚህም ድንበርን በጋራ መጠበቅ የሚል እንደሚገኝበትም ታውቆዋል፡፡

አልበሽር ወደ ኢትዮጵያ በመጣበት ወቅት የተለያዩ የምዕራብ ሀገራት አምባሳደሮችና ዲፕሎማት እንዳይገኙ የደህንነት ኃይሎች የከለከሉ ሲሆን ሁለት ቀናት በሀገር ውስጥ በቆየባቸው ጊዜ እጅግ ከፍተኛ ጥበቃ ሲደረግለት እንደነበረም ታውቆዋል፡፡

EthioLion.Com